

# የምግብ ቤት ማገገሚያ ገንዘብ ድጋፍ

የአሜሪካን ማዳን እቅድ ሕግ SBA የሚያስተዳድረዉ የ$28.6 ቢሊዮን Restaurant Revitalization Fund አቋቁሟል። ብቁ የሆኑ ድርጅቶች ከቀረጥ ነጻ፡ የ2020 ጠቅላላ ገቢን ከ2019 ጠቅላላ ገቢ በመቀነስ የሚሰላ፡ ከወረርሽኝ የተያየዘ የገቢ ኪሣራ እኩል የሆነ የፌዴራል ገንዘብ ድጋፍ መቀበል ይችላሉ።

የገንዘብ ድጋፎቹ በደመወዝ፣ ሞርጌጅ፣ ኪራይ፣ ግልጋሎቶች፣ እና SBA ሥራዎችን ለማስቀጠል ወሳኝ ናቸዉ ብሎ የወሰናቸዉን ሌሎች ወጪዎች ላይ መዋል አለባቸዉ።

ብቁነት፡ ምግብ ቤት፣ ምግብ ማቆሚያ፣ የምግብ ጭነት መኪና፣ የምግብ ጋሪ፣ ምግብ አከፋፋይ፣ ሳሎን፣ ሞቴል፣ መጠጥ ቤት፣ ላዉንጅ፣ ቢራ መጥመቂያ፣ መቅመሻ ክፍል፣ እና/ወይም መጠጥ ክፍል።

ለምግብ ቤት ማጠናከርያ ገንዘብ ድጋፍ ፍላጎት ያላቸዉ ድርጅቶች የሚከተሉትን ማዘጋጀት አለባቸዉ፡ 2019/2020 የሂሳብ መዛግብት።

በመጪዉ ሳምንታት ከ SBA ዝርዝር መረጃ እንጠብቃለን።

**ለመጀመሪያ 21-ቀን ጊዜ፡ SBA በሴቶች፣ ጦር አባቶች፣ ወይም ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት/ጫና ለደረሳባቸዉ ባለቤትነት ለተያዙ አነስተኛ ድርጅቶች ቅድሚያ ይሰጣል።**

Seattle Office of Economic Development

# የደመወዝ ጥበቃ መረሃ ግብር (PPP)

የደመወዝ ጥበቃ መረሃ ግብር (PPP) በኮቪድ-19 ቀዉስ ለተጎዱ አነስተኛ ድርጅቶች ላይመለስ የሚችል ብድር ይሰጣል።

ኣነስተኛ ተቋሞች፡ ሰራተኞቻቸው ቅጥር ሆነው መቀጠል እንዲችሉ PPP እንደገና ተከፍተዋል።

ብቸኛ የድርጅት ባላቤቶች፣ ገለልተኛ ኮንትራት ሠራተኞች እና ራሳቸዉን ቀጥሮ የሚያሰሩ ግለሰቦች የጨመረዉን የብድር መጠን መጠቀም ይችላሉ።

የግለሰብ ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (ITIN) ያላቸው የስደተኞች እና ሬፍዩጂዎች አነስተኛ ንግድ ባለቤቶች ለ **PPP** ማመልከት ብቁ ናቸው።

በ **60%/40%** ስንጥቅ መሠረት ብድሩ **100%** ምሕረት ሊደረግለት ይችላል፡

- ቢያንስ የብድሩ **60%** የሰራተኞች ደመዎዝ ለመክፈል ከዋለ
- ከብድሩ እስከ **40 %** የሚያክል ለኪራይ፣ ሞርገጅ፣ ወለድ፣ ዩቲሊቲ (ኤለትሪክ፡ ውኃ... ወዘተ) ክፍያ ከዋለ፡
- ብድሩ ሰፋ ባለ መልኩ ለመጠቀም፡ ለስራ ማስኬጃ፣ በንብረት ለደረሰ ጉዳት፣ የዕቃ ኣቅራቢዎች ወጪ እና የሰራተኛ ጤና/ጥበቃ ወጪዎችን ያጠቃልላል።

## የማመልከቻው የጊዜ ገደብ ግንቦት 31, 2021 ነው

## ለ PPP ለማመልከት ወይም ለእርስዎ እና ለአነስተኛ ንግድዎ ምን የፌደራል ድጋፍ ምንጮች (ሪሶርስ) እንደሆኑ ለመረዳት እገዛ ይፈልጋሉ?

ድጋፍ ለማግኘት የሲያትል የኢኮኖሚ ልማት ጽሕፈት ቤት (OED) በ 206-684-8090 ወይም OED@seattle.gov ያነጋግሩ። የቋንቋ ትርጉም ድጋፍ አለ። ለበለጠ መረጃ እዚህ ጠቅ ያድርጉ።

**OED ለሁሉም የሲያትል የተለያዩ ማህበረሰቦች ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ተደራሽነት በማስተዋወቅ መላውን ከተማ የሚጠቅም ኢኮኖሚ ለመገንባት ቁርጠኛ ነው ።**

